# "ትኩረት"

# ቁ 3

# የቅዱስ ሚካኤል ዳላስ እጣ ፈንታ

ከዚህ ቀደም ሁለት ተመሳሳይ ጽሁፎች አውጥተናል። ጉዳዩ የዳላስ ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራልን ከምእመናኑ ነጥቀው ለጳውሎስ የእጅ መንሻ ለማድረግ ከሶስት አመት በፊት በማህበረ ቅዱሳን፤ በወያኔ ደጋፊወችና አባላት የተጀመረው እርብርቦሽ ዛሬ መልኩን ለውጦ በማስፈራራትና በምእመናኑ መካከል ያልሆነ የሐሜት ዘመቻ በመክፈት በአማኒያኑ መካከል መተማመን እንዲጠፋ መጠነ ሰፊ የስም ማጥፋት ዘዴአቸው ሳይሳካ ቀረ። በተመሳሳይ መልክ ከሶስት አመት በፊት በሁለት ቀሳውስት (በርእሰ ደብር ሞገስና በቄስ ሰብስቤ) የእምነት ቤታችንን ለመክፈል የተሞከረው እና ንጹሐን ምእመናንን ተበድለናል በሚል የሐሰት እሮሮ ድጋፍ በማግኘት ለመከፋፈል የታሰበው ሙከራ ሳይሰራ ሲቀር ዳግመኛ መልኩን ለውጦ ዛሬ በማወቅ ወይም ባለማወቅም ይሁን የቆዩ ለቤተክርስቲያኑ እንደጠባቂ እንቆጥራቸው የነበሩ ትቂት ግለሰቦች የእምነት ቤታችንን ለማጥፋት ከተነሱት ጋር በመሆን በአባላት ተመርጠው በተቀመጡ የአስተዳደር ቦርድ አባላት ላይ የተከፈተው የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ምንም እንኩአን ፍሬ ቢስ ቢሆንም መመኑን በእጅጉ አሳዝኖአል። የስም ማጥፋት የአሉባልታና እርስ በእርስ የማጋጨቱ ስልት ሳይሰራ ሲቀር ወያኔ በአዲስ ቅርጽና ይዞታ የመጨረሻ ሙከራውን ለማሳካት መላ ቤተክርስቲያኑን ለክስ አቅርበውታል።

እንደሚታወቀው ወያኔ/ኢሕአዴግ በምርጫ 1997 እርቃኑን ቀርቶ እውነተኛ ባህርይውና ቆሻሻ ገመናው በወዳጆቹ ምእራባውያን ፊት ከተሰጣ ወዲህ በዲያስፖራ (Diaspora) በስደት የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ዜጋ ለመከፋፈል እና ለመቆጣጠር ያመቸው ዘንድ ከውጭ ተባባሪወቹ (experts) በተሰጠው የማፍረስ እረቂቅ በመደገፍ ለህፍረት የዳረገውን Diaspora በቁርጥ ለመከፋፈል 60 (ስድሳ) ገጽ እረቂቅ ለቅጥረኛ ዲፕሎማቶቹ በመመሪያ አባሪ በመላክ ተፈጻሚ ይሆን ዘንድ ባጀት መድቦ ተንቀሳቅሱአል።

የዚህ እኩይ ተግባር ሰለባ የሆነው የዳላስ ቅዱስ ሚካኤል ደብር ምእመናንና አስተዳደር ቦርድ ነው። ከዚህ በፊት በ 2006 እና በ 2008 እንዳስገነዘብነው። ቤተክርስቲያኑን ቢችሉ አቡነ ጳውሎስ ከሚመሩት ሲኖዶስ ስር ማድረግ አለበለዚያ

መረጋጋት እንዳይኖር ምእመኑን እርስ በእርስ ማጋጨት፤ ሐሜትና የስም ማጥፋት በጠንካራ ግለሰቦች ያነጣጠረ ቅስቀሳ ማካሄድ የተያዘ መላ ሆኖ ቆይቶአል። ቆርጠው የተነሱት ወያኔወች በየቀኑ ስም አጥፊ ወረቀቶች መበተን አንደኛው ተግባራቸው ሆኖአል። ይህ ስልታዊ የማባላት የመከፋፈል ዘዴ እንዳለ ሆኖ በቅርቡ ደግሞ ቤተክርስቲያኑን ከሰው ፍርድቤት አቅርበዋል። እነዚህ ሀፍረተ ቢስ ወገኖች ለአቡነ ጳውሊስ የገቡትን ቃል ለመፈጸም ያዋጣል ያሉትን ሁሉ ወያኔአዊ የመከፋፈል ዘዴ ያሉባልታ ስም አጥፊ ወረቀቶች ከመበተን እስከ ፍርድ ቤት የሚያደርስ ተግባራትን አከናውነዋል። በእለተ ማክሰኞ April 14 ቀን የቀረበው የዳላስ ካውንቲ ዳኛ ክሱ መሰረት አልባ ነው ብሎ ቢዘጋውም፤ ዛሬም መልሰው ለፍርድ እንደሚያቀርቡን በሚበትኑአቸው ወረቀቶች ለመረዳት ችለናል።

ከዚህ በፊት መላ በውጭ የሚኖረው ዜጋ እንዲያውቀው ባወጣነው መጣጥፍ መሰረት። አቶ ሕላዊ ዮሴፍ የወያኔው አንድ አካል ለሆነው ባአዴን ለተባለ መጋዣ ድርጅት አመራር የሆነው ግለሰብ ከአማራው ክልል ምናምን ጋር መጦ በነበረበትና የዳላስ ኢትዮጵያውያን ባደረጉት የተቃውሞ ሰልፍ አፉን መከፈት ያልቻለው የወያኔ ሹመኛ፤ በድብቅ ሹመት ሰጦ መሄዱን አስታውቀን ነበር። <u>ይህም አምስት የኮሚቴ አባላት ያሉበት የኮንሰንሰስ (consensus committee) የተባለ በወያኔ የሚታወቅ፤ ስራና ተግባሩ በውጭ ነዋሪ የሆነውን ኢትዮጵያውያዊ ዜጋ ለመቆጣጠርና ለመከፋፈል የተዘየደ ኮሚቴ በከተማችን መመስረቱን በድህረ ገጾች አሳውቀን ነበር </u>። ይኸን ስንል በነጻ አገር እንዴት መቆጣጠር ይቻላል ይባል ይሆናል። እርግጥ ነው ያለንበት አገር ነጻ እና ፍትህ እረት ያለበት ቢሆንም ሰው በተፈጥሮ ማህበራዊ ኑሮ አፍቃሪ (social animal) እንደሚሉት ማለት ነው፤ በስብስብ ስለምንኖር። በማህል ገብቶ ቢቻል ነዋየ አፍቅሮት ያለውን ቤትና መሬት ይሰጥሀል በማለት ወደነሱ መሳብ። በዚያ የማይደለለውን እርስ በእርስ ማናከስ በመሆኑ ዛሬ በዳላስ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን እየተፈጸመ ያለው የወያኒያዊ የመከፋፈል ተግባር ላለፉት ሁለት አስርት አመታት የገነባነውን የእምነት ቤት ለማፍረስ አስፈጻሚወች ደፋ ቀና እያሉ ለመሆኑ እያየን ነው። የዚህ ተግባር ተሸካሚ እና አስፈጻሚ የሆኑት ደካሞች ትቂቶች ትናንትም ሆነ ዛሬ በማይገጥም ባህሪይያቸው ከኮሚውኒቲው ጋር ሲጋጩ የኖሩ አንዳንዶቹ አንቱ የተባሉና ያላቸው ሐብትና ንብረት ያልበቃቸው እግር ወደመሬት እንደሚሉት አሁንም ለንዋይ ምንም ነገር ለማድረግ ዝግጁ የሆኑ ግለሰቦች አሉባቸው። ከነዚህ ውስጥ ቀደም ባለው ጊዜ ተቃዋሚ ነን ብለው ያዙን ልቀቁን ይሉ የነበሩ ሲሆኑ። ዛሬ መለኛው ወያኔ የህዝብና ያገር ሐብት የሆነውን መሬት ለግሶአቸው በፈለጉት አይነት እና ባሰቡት ጊዜ እየወጡ እየገቡ በተቸራቸው ሀብት ንግድ በመያዛቸው መልካም መጋዣ ሆነዋል። አሳዛኙ እና አስገራሚው ከዚህ ቀደም በደርግ አስተዳደር ከፍተኛ ቦታ ኖሮአቸው ህዝብን እና አገርን የበደሉ እና ለዚያ ንስሐ ገብቻለሁ ይሉ የነበሩ አይወግኑ ወገን ዛሬም በድጋሚ ወግነው ያ የተፈጠረባቸው የአድርባይነት እትብት ጎትቶ ከወያኔ እግር ስር ደፍቶአችዋል። በሚያውቁበትና በለመዱት ካድሬአዊ ስራ ሽር ጉድ ብለው የወያኔ ባለስልጣናትን ተቀባይም ደረሱ። እንዲህ አይነት ጉዶችም አገር ደርሰው እግር ስመው ከተመለሱ

በህዋላ ለዘመናት በስደት አገራችን ሰብሳቢ የሆነውን የዳላስ ቅዱስ ሚካኤልን የመቀማት አለያም ማፍረስ በሚለው የወያኔ አላማ ተመርተው ቤተክርስቲያኑን ፍርድቤት አቅርበውታል። ይህን አስከፊ ሰይጣናዊ ተግባር እንዲፈጽሙላቸው የዋሃን የሆኑ እና በቅን ሲያገለግሉ የነበሩትን ጭምር አሳስተው ከወገን እና አብረው ከኖሩት ማህበረሰብ ለይተዋቸዋል። በሁዳዴ ጾም ተከሶ በህማማት ፍርድቤት የቀረበው ቤተክርስቲያንና ምእመናን፤ ክሱ በቂ ምክንያት የለውም በማለት የተዘጋ መሆኑ ለጊዜውም ቢሆን እፎይታን ሰጦናል። የሆነው ሆኖ በአፍራሽ ደመኛ የተጀመረ በመሆኑ ይህ የመጀመሪያ የፍርድ ቤት ውሳኔን ለማስለወጥ መንጋ የወያኔ እና ያባ ጳውሎስ ሰራሽ ግለሰቦች ይግባኝ ማለታቸውን ዜናው ደርሶናል። እዚህ ላይ ዛሬም በድጋሚ ጎራ እንዲለዩ የምንፈልግባቸው ግለሰቦችም ሆነ ስብስቦች አሉ። በዚህች አጭር ጽሁፍ የምንጠይቀውም ወያኔ አይደለንም። ጳውሎስን አንደግፍም እያሉ ግን የዚሁ አፍራሽ ስብስብ በሐሳብና በመንፈስ ተባባሪ የሆኑ ሁሉ ጊዜው አሁን ስለሆነ በማያምኑበት ገብተው ለወደፊት ለሚሰራው መጥፎ  ተግባር አጋዥ ከመሆን እንዲቆጠቡ እንጠይቃለን። ቤተክርስቲያኑ የግል ሳይሆን የምእመናኑ ስለሆነ አጉል ምክንያት እያቀረቡ ለጠላት ዱላ አቀባይ መሆን እንዲቆም ይገባል እንላለን።

ያለንበት አገር ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርና የምርጫ ስራት እንደአስተማረን፤ አስተዳደር ውስጥ እንኩአን ለመግባት የሚፈልጉ ቢኖሩ የብዙሐንን ይሁንታ መቀበል እና ለወደፊት የብዙውን ድምጽ አግኝቶ ለመመረጥ መስራትን የጠበቅባቸዋል እንጅ ለጠላት አባሪ ተባባሪ ሆኖ ጸጸት ውስጥ ምውደቅ መልካም ስራ አይደለም እንላለን። ሌላው ለማስገንዘብ የምንወደው ወያኔና ደጋፊወቹ፤ አፍቃሪ ጳውሎሶችን ጨምሮ በምንም መልክ የብዙሐን ድምጽ ሊያገኙ እንደማይችሉ ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው። ይህን እያወቁ የጎን የስም ማጥፋት ወረቀቶች እየበተኑ ህዝብን ማሳዘን ግን የበለጠ ያስገምታል እንጅ ድጋፍ የሚያስገኝ ተግባር አይደለም። እዚህ ላይ ማስገንዘብ የምንወደው ኣባ ጳውሎስ የኦርቶዶክሳዊውን ስራት ያጎደፉ ናቸው እያሉ ከነዚህ ከተሹአሚ ፓትርያርክ ደጋፊወች ጋር የሚተባበሩትን፡ ያለቦታችሁ ነው ተመለሱ ማለት እንወዳለን።

ማህበረ ቅዱሳኑን አስመልክቶ የተነሱ ጥያቄውችም ሆነ በደብሩ አስተዳደርና በምእመናን የተደገፉት እንደሚከተለው እንጠቅሳለን።

1. የማህበሩ አባላት በአለንበት አገር የ nonprofit status ወይም 501c3 ፈቃድ ያላቸው በመሆኑ።
2. ቤተክርስቲያናችንም ተመሳሳይ ፈቃድ የያዘ የእምነት ድርጅት በመሆኑ
3. ማህበሩ (ማህበረ ቅዱሳን) በሰንበት ት/ቤቶች ስር የተዋቀረና አቡነ ጳውሎስ የበላይ አስተዳዳሪው ስለሆኑ።

EthioLion.Com

4. ቅዱስ ሚካኤ ዳላስ የአቡነ ጳውሎስን መንበረ ስልጣን ህጋዊ ነው ብሎ ስለማያምን እና አመራራቸውን ስለማይቀበል።

5. ሁለት ተመሳሳይ የእምነት ማህበራት አንዱ በሌላው ስራና ተግባር ተሳታፊ መሆን አይችልም አይገባም።ያ ቀርቶ አራጊ ፈጣሪ ከሆነ የጥቅም ግጭት (conflict of interest) የሚባል ነገር ስለአለ የቤተክርስቲያኑ አባል ቢሆኑም የስራ ሐላፊነት ግን መውሰድ አይቻላቸውም።

ይህ ከላይ የጠቀስናቸው ዝርዝር ነጥቦች በእኛና በማህበሩ መካከል ስለሚኖሩ ግንኙነቶች በግልጽ የሚአያስረዱ ስለሆነ ይህን ያልተረዳ የማህበሩ አባል ካለ ጥያቄወች ቢኖሩት ፍርድ ቤት ሳይሆን የሚፈታቸው ምእመናኑ እና ያስተዳደር ቦርዱ ስለሆነ፤ ጠበቃ ይዞ ገንዘብ ማውጣቱ ፋይዳ የለውም እንላለን።

ከዚህ አንጻር ሌላው ልንጠቅሰው የምንወደው፤ ዛሬ በከተማችን ጳውሎስን የተቀበለ ቤተክርስቲያን እራሳቸውን በግልጽ ባሳወቁ የወያኔ አባል ቄስ ስለተከፈተ ያባት ጥያቄ ያነሱ ሁሉ ወደዚያው ቢሄዱ ይቀላል ባይ ነን።

ይህ ጽሁፍ በዳላስ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን "ትኩረት" በሚል በአስፈላጊ ጊዜ በምትወጣ መጣጥፍ ስር የተሰባሰቡ ዜጎች ናቸው።

ስብስቡ የኢትዮጵያን ተንሳኤ በሚመኙና በሚደግፉ ዜጎች የተመሰረተ ነው።

ይህን ማሳሰቢያ ያወጣንበት ሰአት፤ ቤተክርስቲያናችን በተከሰሰበት እና ለእምነታችን አስቸጋሪ በሆነበት ጊዜ ነው።

እውነት ለጊዜው ብትዳከምም የማታ ማታ አሸናፊ ትሆናለች።

EthioLion.Com